ሁለት ሴት ልጆችን እስኪደርሱ ድረስ የተንከባከበ ሰው የትንሳኤ ቀን እኔና እሱ እንዲህ ሆነን ይመጣል።" ጣታቸውንም አጣበቁ።

ከአነስ ቢን ማሊክ (ረዲየላሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ አሉ፦ "ሁለት ሴት ልጆችን እስኪደርሱ ድረስ የተንከባከበ ሰው
የትንሳኤ ቀን እኔና እሱ እንዲህ ሆነን ይመጣል።" ጣታቸውንም አጣበቁ።» [ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ሁለት ሴት ልጆችን ወይም እህቶችን የተለገሰና ለአቅመ ሄዋን እስኪደርሱ ድረስም ለነርሱ ቀለባቸውን፣ በመልካም ማነፁን፣ ወደ መልካም መጠቆሙን፣ ከመጥፎ መከልከሉንና የመሳሰሉትን ሀላፊነቶች እየተወጣ የተንከባከባቸው ሰው የትንሳኤ ቀን እርሱና ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንደዚ ሆነን ይመጣል ብለው መጠቆሚያ ጣታቸውንና መሀል ጣታቸውንም አጣብቀው አሳዩ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/3360